# ማስታወቂያ

## ለትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ተጠቃሚዎች በሙሉ!

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣ የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 19/2007 መሰረት ከመታወቂያ ዕድሳት ጋር በተያያዘ ጊዜያቸውን ጠብቀው ያላሳደሱ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የተጣለባቸውን የቅጣት መጠን እንዲከፍሉ ተወስኖ የነበረ መሆኑ፣ ከዚያም ከተገልጋዮች ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው የቀረበውን ቅሬታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ያለቅጣት የሚታደስበት የእፎይታ ጊዜ እንዲኖርና ይህም እስከ ሐምሌ 30/2007 ዓ.ም እንዲቆይ ተወስኖ እንደነበር ይታወሳል፡፡

አሁንም በጊዜ ገደቡ ቀርበው ያላሳደሱ ወገኖች ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው በተደጋጋሚ ጥያቄ እያቀረቡ ስለሆነ የጊዜ ገደቡን ማራዘም አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም የተወላጅነት መታወቂያን ለማሳደስ የተቀመጠው ቀነ ገደብ ላልተወሰነ ጊዜ ያለቅጣት እንዲራዘም የተወሰነ በመሆኑ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት የትውልድ መታወቂያ እድሳት እንድትፈፅሙ እናሳስባለን፡፡